# ኢትዮጵ

ቅጽ 1 ቁጥር 6 (ሐምሌ) 1985






## የመጨረሻው ቃለ ምልልስ

### ከልዑልሰገድ ኩምሳ የደከመ አንደበት ጋር




## መናኟ ዶክተር

ከአትላንታ ዩኒቨርስቲ ወደዋልድባ ገዳም
እስከራሚያው የምነና ታሪክ

«ኢሕአዴግ . . . ስለ ሰላም የሚወያይ ስብሰባ አገር ውስጥ አይካሄድም ካለ. . . የሚጋለጠው እሱው ነው።»

ዶ/ር ነገደ ጉበዜ

- ስለ ጥቅምቱ ጉባዔ

# ለጥቅምቱ የአዲስ አበባ የሰላምና ዕርቅ ጉባዔ

## (ከሰላምና ዕርቅ በኢትየጵያ ሀገር አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊ/መንበር ከዶ/ር ነገደ ጎበዜ ጋር የተካሄደ ቃለ ምልልስ)

ተቃዋሚ ድርጅቶች በመጋቢት ወር 1993 ዓ.ም. በፓሪስ ከተማ ስብሰባ አካሂደው የሰላምና አስተባባሪ ኮሚቴ በማቋ ቋም አንድ ሀገር አቀፍ ጉባዔ እንዲጠራ መወሰናቸው የሚታወቅ ነው። የዚሁ የሰላምና የዕርቅ አስተባባሪ ኮሚቴው ጽሑፍ እንደሚገልፀው በሚያዚያ ወር 1985 ዓ.ም. በለንደን ውስጥ በተካሄደ ስብሰባ ላይ ከጥቅምት 5-9 ቀን 1985 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አገር አቀፍ የሰላምና የዕርቅ ጉባዔ ለማካሄድና ለዚህ "...አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ መንግሥታዊም ሆነ በተቃዋሚነት የተሰለፉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ እንዲሁም ከፖለቲካ ውጭ የተደ ራጁ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ድርጅቶችና የማህበራት ተወካዮች ..." እንዲሳተፉበት በደብዳቤ ጥሪ አቅርቧል። ኮሚቴው በዚህ ጉባዔ ላይ "የኢሕአዴግ ተሳትፎ መገኘት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል" ብሎ ያመነበት መሆኑን ገልፆ ለሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንት ለአቶ መሰስ ዜናዊም አንድ ደብዳቤ እንዲፃፍ መወሰኑን ጨምሮ ይጠቁማል። ስለዚህ እነዚህን ጉዳዮች መሠረት በማድረግ የሉሲ ዝግጅት ክፍል ለሰላምና ዕርቅ በኢትዮጵያ ሀገር ኣቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊ/መንበር ለዶ/ር ነገደ ጎበዜ መጠይቅ አቅርቧል።

ጥያቄ:- በፓሪሱ ኮንፈራንስ የተሰየመው የብሔራዊ ኮንፈራንስ አስተባባሪ ኮሚቴ ከጥቅምት 5 እስከ 9 1986 ዓ.ም. ድረስ አዲስ አበባ ብሔራዊ ኮንፈራንስ እንዲካሄድ ለፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ በደብዳቤ መጠየቁ በሰፊው ይነገራል። የተገኘውን መልስ ቢገልጹልን?

መልስ:- ጉባኤው እንዲደረግ ፈቃድ ጠይቀን አልጻፍንም።። ኢህአዴግ በጉባኤው ላይ እንዲገኝ ጠይቀንና በዚሁ ጉዳይ እንድንወያይ ሃሳብ አቅርበን ነው የጻፍነው። የሆነ ሆኖ እስካሁን ድረስ ለደብዳቤያችን መልስ የለም።

ጥያቄ:- በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ እንዲካሄድ የታቀደው ብሔራዊ ኮንፈራንስ ትኩረቶችና ዓላማዎች ወይም አጀንዳዎች ምንድን ናቸው? የኤርትራን ወቅታዊ ሁኔታስ ይመለከታል? እንዴት?

መልስ:- አጀንዳውን እንኳን ይፋ ልናወጣው ቀርቶ አሁን ባለንበት ደረጃ እኛም አናውቀውም። ይህ ጉባኤ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ግልጽ፣ ያልተድበሰበሰና ዲሞክ ረሲያዊ እንዲሆን እንፈልጋለን። እኛው አጀንዳ አውጥተን፣ በዚህ አጀንዳ ላይ የሚደረጉትን ውሳኔዎች እኛው በቅድሚያ አጽድቀን፣ የጉባ ኤውን መግለጫዎች እኛው በቅድ ሚያ አዘጋጅተን ሁሉን ነገር ከቆላ ለፍን በኋላ ሰውን ሁሉ እንደ አዳራሽ ውስጥ ዘግተን "ካሁን ወዲያ መውጣት የለም፣ ይኸው በዚህ አጀንዳ ተወያዩ፣ ይህ መግለጫ በእናንተ ስም ይውጣ" ማለት አንፈልግም። ይህን ካደረግን ካለፉት ስህተቶች ምንም አልተማርንም ማለት ነው። ጉባኤውም ውጤት አይኖረውም። የምንሠራው በፓሪሱ ጉባኤ እንዲደረግ ነው። ተሳታፊ ሁሉ በቅድሚያ የአጀንዳ ነጥብ በጹሑፍ እንዲልክ ይጠይቃል። ከዚህ ሁሉ ተቀናብሮ አንድ የአጀንዳ ረቂቅ ሃሳብ ለህዝብ ይፋ ይሆናል። ለተሳታፊዎችም ይላካል። ሁሉም በየድርጅቱ ተወያቶበት ይመጣል።በኤርትራም ጉዳይ የተለየ አሠራር አይኖርም።ተሳታፊ ድርጅቶች ይህ ጉዳይ በአጀንዳ ይያዝልን ካሉ ይያዛል። በበኩሌ ሳስበው ይህንን ጥያቄ የሚያነሱ ድርጅቶች አይኖሩም ብዬ መገመት ስለ ሚያቅተኝ የኤርትራም ጉዳይ አንድ የውይይት ነጥብ እንደ ሚሆን ይሰማኛል። ይህ ስለተባለ ግን ጉባኤው ዓላማ የለውም ማለት አይደለም። አለው። ከዚያ በፊት የነበረውን ሁኔታ ወደጎን ትተን ከዘመነ መሳፍንት ወዲህ እንኳን ባሉት 250 ዓመታት ሃገራችን በአጠቃላይና በተከታታይ የአስር ዓመት ሰላም አግኝታ የማታውቅ አገር ነች። ዛሬም ቢሆን ጦርነቶች አላቆሙም። የእርስ በርስ ጦርነት ለአንድ ህብረተሰብ በሙሉ ሽንፈት እንዳልሆነ ሁሉ ብቻቸውን በአሸናፊነት የወጡ የሚመስላቸው ኃይሎች አሉ። ግን በዚህ ሁኔታ መጣ የሚባለው ሰላም የአሸነፍን ባዮች ሰላም ነው። እጅግ ወገነኛ ሰላም ነው። በዚህም የተነሳ በቋፍ ያለ ሰላም ነው። እስካሁን ድረስ በሃገራችን በረሃብ የተጎዱ የሚል አነጋገር ነበረን። በጦርነት የተጎዱም እንል ነበር። አሁን ደግሞ ይህ ወገነኛ ሰላም የፈለፈላቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ "በሰላም የተጎዱ" ልንላቸው የምንችል በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አሉ። በእውነት አንዳንዴ ሳስበው፣ ያሉትን የፓለቲካ፣ የሶሻል፣ የኢኮኖሚ፣ የሞራልና የህልውና ቀውሶችና ችግሮች ሳይ ሃገራችን በዚህ ዓለም ካሉ ችግሮች ከተገቢ ድርሻዋ በላይ የተሸከመች ይመስለኛል።። እነዚህ ችግሮች እዚህ ያደረሳቸው ለውስብስብ ችግሮች ቀላል መፍትሄዎች እየተጠቀሙ፣ እነዚህን መፍትሄዎች ደግሞ በኃይል በህብረተሰቡ ላይ ለመጫን የተደረጉት ሙከራዎች ናቸው። አሁንም ተረኛው "አሸናፊ" ኃይል ከዚህ የተለየ መፍትሄ ማቅረብ አልቻለም። የሃገራችን ውስብስብ ችግሮች ቀላልና አንድ ወጥ መፍትሄ የላቸውም። ቢኖር እስከዛሬ ይሰማ ነበር። ይህ እየታወቀ በአንድ ወቅት በተለያየ የታሪክ፣ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ አጋጣሚዎች የጦር ድል የተጎናጸፈ ኃይል ይህንን ጊዜያዊ የጦር ድል ወደዘላቂ የፖለቲካ ድል ለመመንዘር በኃይል ከሞከረ፣ የሽግግሩ ሂደት መጭው የሃገሪቱ የፓለቲካ አወቃቀር፣ መጭው ህገመንግሥት መጭው ምርጫ የአሸናፊዎችን ይዞታ ለማጠናከር ብቻ

ከተቀየሰ ያው ተመልሰን እዛው ጦርነት አዙሪት ውስጥ መዘፈቅ ይሆናል። ከነዚህ ሁሉ ነጥቦች ስነሳ መጨውን ጉባኤ ነገ ጥቅምት 1986 ዓ.ም. መንግሥትን ተቃዋሚ ኃይሎች በሀገሪቱ ያለውን የፖለቲካ ስልጣን እንዴት እንቀራመተው በሚል ጥያቄ ላይ አያተኩርም። ኢህአዴግ ሃገሪቱን ለሚቀጥለው ምርጫ ለማ መቻቸት ከሚያደርገው መሯሯጥ ጋብ ብሎ ኢትዮጵያን ለሚቀጥለው ትውልድ የምናመቻችበትን የሰላም፣ የዲሞክራሲ፣ የእኩልነትና አንድነት መሰረት ስለምንጥልበት ዘዴ እንወያይ ነው የምንለው። ይህንን መሠረት በጋራ ከጣልን በኋላ ብቻ ነው በዚህ ክልል ውስጥ ስለምርጫም ሆነ ስለፖለቲካ ሥልጣን ማሰሳሰል መጀመር ያለብን። **እስቲ ሁሉም ይገናኝና ስለሽግግሩ ሂደት ይወያይ። እስቲ ቆም ብለን ይህንን የርሃብና የጦርነት አዙሪት የምንሰብርበትን ዘዴ በመመካከር እንሻ፤ መጭው ጉባኤ ከዚህ ሌላ ዓላማ አይኖረውም።**

<u>ጥያቄ</u>:- በተለይ የሽግግሩ መንግሥት ዋነኛ አካል የሆነው ኢህአዴግ እናንተ ያሰባችሁት ዓይነት ኮንፈራንስ በአዲስ አበባ ወይም በሃገር ውስጥ እንዲደረግ አልፈቀደም፤ እኔም ተሳታፊ አልሆንም ወይም ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ አወንታዊ መልስ ቢሰጥ በሁለቱ አቅጣጫዎች ሊከተሉ የሚችሉ በጎና አሉታዊ ውጤቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ አስተባባሪ ኮሚቴው ይገምታል?

<u>መልስ</u>:- ተራ በተራ እንሂድ። ከሁሉም ለሃገራችን የሚበጀው ኢህአዴግ በጉባኤው ላይ ቢሳተፍ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አሁን እንደተባለው እዚህ ስበሰባ ላይ አልገኝም ቢልስ? በኛ ግምት ጉባኤው ያለኢህአዴግም መደረግ ይኖርበታል። እርግጥ የኢህአዴግ አለመገኘት የጉባኤውን በጎ ውጤት እንደሚቀንሰው ግልጽ ነው። አሉታዊ ውጤቱን ግን ማጋነን አያስፈልግም። እርግጥ በሃገራችን ከላይ ባወሳሁት መልክ የርሃቡንና የጦርነትን አዙሪት ለመስበር የሚደረገውን ትግል ይበልጥ ያወሳስበዋል፣ ይበልጥ ያረዝመዋል። ግን ደግሞ የዓለም መጨረሻ አይሆንም። ኢህአዴግ ፓሪስ አልገኝም ስላለ የፓሪሱን ጉባኤ አላስቀረውም። አወንታዊ ውጤቱንም ሆነ ታሪካዊነቱን እምብዛም አልቀበ ለውም። ስብሰባው ያለ ኢህአዴግ ቢደረግ ምን ይዞ ጉዞ አይሆንም ወይ የሚሉን አሉ። እኛ አይሆንም ነው የምንለው። ዛሬ በሃገራችን ሁኔታ ከፍተኛ ውዥንብር አለ። ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁኔታ የሚወለደው ከእንዲህ ዓይነቱ ውዥንብር እንደሆነ የሱማሌያ አሳዛኝ ሁኔታ በደንብ የሚያሳይ ነው። ዛሬ በሃገራችን ዘላቂ ሰላም የሚሉ፣ አስተማማኝ ዲሞክራሲ የሚሉና በዲሞክራሲያዊ ሂደት ወደዲሞክራሲ ሥርዓት እንሸጋገር የሚሉ ኃይሎች ስፍር ቁጥር የላቸ ውም። ውዥንብሩ የሚፈጠረው ሁሉም በየፊናቸውና በመሰላቸው መታገላቸው ነው። እነዚህ ኃይሎች ተሰባስበውና ተወያይተው ቢያንስ ሽግግሩን በሚመለከት እጅግ አነስተኛ የሆነ የጋራ አቋም ቢይዙ ለሃገራችን ታሪካዊ ድል ይሆናል። ከኢትዮጵያ 10ሺ ኪሎ ሜትር ርቀው፣ 7 የፖለቲካ ድርጅቶች ያደረጉት ጥሪ በውስጥም በውጭም ምን ያህል እንዳስተጋባ አይተናል። በህዝባችን ዘንድ ምን ያህል ተስፋ እንደቀሰቀሰ ተገንዝ በናል። ከነዚህ ቁጥራቸው የላቀ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ እነሱ ብቻም ሳይሆኑ የሲቪል ሶሳይቲው ተወካ ዮች፣ ፖሪስ ሳይሆን አዲስ አበባ ተሰብስበው ስለሃገራቸው ቢወያዩ፣ የሽግግሩን ዲሞክራሲያዊ ሂደት በሚመከመት አንዳንድ ነጥቦች ላይ ቢስማሙና ለዚህም በጋራ ለመታገል የሚያስችላቸው እንደፓሪሱ የ7 ሰዎች ኮሚቴ ሳይሆን ሁሉም የሚወከልበት አንድ አካል ወይም ካውንስል ቢመሠርቱ ይህ ጉባኤ የሚያገኘው አስተጋብኦና የሚያ ስገኘውን ጥራት እናንተው ገምቱት። ሌላው ቀርቶ ከጥቅምት በኋላም ጉባኤው ላይ ካልተገኘው የኢህአዴግ መንግሥትም ጋር ለመወያየት ከኢህአዴግ ውጭ ያለውን ህብረተሰብ የሚወክል አካል መኖሩ ትልቅ ርምጃ ይሆናል። **ሶስተኛው ኢህአዴግ እኔም አልገኝም እናንተም አዲስ አበባ አትሰበሰቡም ቢልስ የሚለው ጥያቄ ነው።** ይህ በእውነቱ ቢያንስ ቢያንስ ከኛ እኩል ኢህአዴግ ሊጨነቅበት የሚገባው ጥያቄ ይመስለኛል። የሰላም ኃይል ነኝ እያለ ውይይት አሻፈረኝ ቢል፣ በሃገራችን ዲሞክራሲ አስፍኛለሁ፣ የሰው ልጅ መብት ተከብሯል፣ የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ የሰው ልጅ መብት መግለጫ በሃገራችን ጸድቋል እያለ፤ ስለሰላም የሚወይ ስብሰባ አገር ውስጥ አይደረግም ካለ በጸረ ዲሞክራትነቱ የሚያጋልጠው እሱው ነው።

<u>ጥያቄ</u>:- ከላይ እንደተጠቀሰው ኢህአዴግ ስብሰባውን አዲስ አበባ ሊደረግ አይቻልም ቢል የተቃዋሚ ኃይሎች ምን ምርጫ ይኖራቸዋል?

<u>መልስ</u>:- ወደዚህ ከመግባቴ በፊት በአንዲት ነገር እንስማማ። **ይህ ጉባኤ በምንም ዓይነት የተቃዋሚ ኃይሎች ስብሰባ አይደለም፤** ከላይ በተጠቀሰው መሠረት የሰላምና የዲሞክራሲ ጉዳይ ያገባኛል የሚልና ከፖለቲካ ውጭም የተደራጀ፣ መንግሥትን የሚደግፍ፣ ከመንግሥት ነፃ ነኝ የሚልም ሆነ ይህንን መንግሥት የሚቃወም ሁሉ እንዲገኝ እንፈልጋለን። እንደዚህም በመሆኑ ሌላው ቀርቶ ኢህአዴግ ባይገኝ እንኳን ይህ ስብሰባ የተቃዋሚ ፖለ ቲካ ደርጅቶች ብቻ ጉባዔ አይሆንም። ኢህአዴግ በጸረ ዲሞክራትነቱ ይህንን ስብሰባ አዲስ አበባ አይደረግም የሚለውን አቋም ለማስተላለፍ በውጭም በውስጥም ሶስት ዋና ዋና ስበቦች ይደራደራል። ጉባኤው ጸረ ቻርተር ነው ይባላል። ዲሞክራሲ ካልን ይህ አያዋጣም። እንኳን ከጥንስሱ ሁሉን ያላካ ተተና አወዛጋቢ የሆነ ጊዜያዊ ሰነድ ቀርቶ ቋሚ ህገ መንግሥትም መቃወም፣ እንዲ ሻሻል፣ እንዲለወጥ እስከናካ ቴው ተሽሮ በሌላ እንዲተካ የፖለቲካ ትግል ማካሄድ ይቻላል። የአሜሪካ ህገመንግሥት ባለፈው 200 ዓመት ከ20 ጊዜ በላይ ተሻሽሏል። ለውጥ እንዲደረግ የተከራከሩ ኃይሎች "ጸረ ህገመንግሥት" እየተባሉ ሳይመቱ። እንዳው ለነገሩስ ቢሆን ዛሬ በኢትዮጵያ ቻርተሩ የሚሰጠውን መብት የሚገፍ ጸረ ቻርተር ሃይል ማን ሆኖ?

**ያውም እንዲህ ይህ በመርህ ደረጃ**

**ነው። ለነገሩማ ስለሰላም ተሰባስበን እንወያይ ሲባል እንዲህ ዓይነቱ ስብሰባ ፀረ ቻርተር ነው ከተባለ፣ በቻርተሩ ስም ከተከለከለ ሰላምና ዲሞክራሲ በአንድ በኩል፣ ቻርተር በሌላ በኩል መሰለፋቸው ነው። ነገሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ወገኖቻችን የሚታሰሩበት፣ የሚጋዙበት፣ ቤት ንብረታቸው የሚፈታበት ሰበብ መሆኑ ያሳዝናል እንጂ በውጭ ወዳጅ ቻቸውም እያፈሩበት የማያነሱት መከራከሪያ ሆኗል።**

ሁለተኛው ነጥብ ሰብሰባውን ጥቂት የስልጣን ጥመኞች መንግሥት ለመገልበጥ የጠነሰሱት ስብሰባ አድርጎ የማቅረብ ነገር አለ። ይህም አላዋ ጣም። አያዋጣም። የፓሪሱ ጥሪ ይህ መንግሥት ወርዶ በሌላ ይተካ አይልም። ተሰብስበን ስለሽግግሩ እንወያይ። ለሃገራችን ሰላምና ዲሞክራሲ የሚሰፍንበትን ዘዴ ተመካክረን እንቀይስ ብቻ ነው የሚለው። ኮሚቴያችን ይህንን ስብሰባ ለማዘጋጀት እንጂ መንግሥት ለመገልበጥ አልተቋቋመም። እርግጥ ሽግግሩ እንዲሳካ ሌላ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ብለው የሚጠይቁ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። ስብሰባውም ላይ ተገኝተው ይህንኑ አቋም ይዘው መከራከር ዲሞክራሲያዊ መብታቸው ነው። **ኢህአዴግና ደጋፊዎቹ ደግሞ ተገኝተው የተያዘው መንገድ ያዋጣል፣ መንግሥት መቀየርም አያስፈልግ፣ የሽግግሩን ወቅት አደራ ሁሉንም አስማምተን እኛው እንወጣዋለን፣ እርግጥ በዚህ በዚህ ይሻሻል ከተባለ አሠራራችን በዚህ በዚህ ሊሻሻል ይችላል ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ።**

ሶስተኛው መከራከሪያ ይህ የጉባኤ ጥሪ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የተለያዩ ክፍሎች ያደረጉትን ጥሪ ሳይሆን የጥቂት ስልጣን ጥመኛ ስደተኞች ጥያቄ ነው የሚለው በቲዎሪ ክርክር ሳይሆን በተግባር መመለስ ያለበት መከራከሪያቸው ነው። ይህንን መከራከሪያ የምናከሽፈው እኛ ሳንሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ኢህአዴግ እስከመጨረሻው ይህ ጉባኤ አዲስ አበባ አይደረግም ቢል አማራጩ ምን ይሆናል የሚል ጥያቄ ቀርቧል። "ለሃገራችን ከመታገል ሌላ አማራጭ የለንም" ብሎ በደፈናው መመለስ ይቻላል። ከዚያም አልፎ ዝርዝር ታክቲክና ስትራቴጂ ማተት ይቻላል። ዋናው ቁም ነገር ግን አሁን እሱ አይደለም። ዛሬ ዋናው ቁም ነገር ይቺን የቀረችውን "የጥቂት ስደተኞች ጥያቄ"፣ "የጥቂት ስልጣን ጥመኞች ሴራ" የምትል መከራከሪያ ማከሸፉና ማጋለጡ ነው። ዋናው የዛሬው ጥያቄ የኢትየጵያ ህዝብ ለእንዲህ ዓይነቱ የሰላም ጉባኤ ያለውን ድጋፍ በገፍና በማ ያሻማ ሁኔታ ለመላው ዓለም የማሳየቱ ጥያቄ ነው። እስቲ መጀመሪያ ተማሪው፣ መምህሩ፣ ጋዜጠኛው፣ ባለ ሙያው፣ ምሁሩ፣ ሠራተኛው፣ ገበሬው፣ ነጋዴው፣ ለሰው ልጅ መብት ታጋዩ፣ የሃይማኖት አባቱ...ለዚህ ጥሪ አወንታዊ መልሰ ይስጥ። እስቲ ሁሉም በመን ቀሳቀስ የኢህአዴግ የውጭ ፕሮፖጋንዳ እንደሚለፍፈው ይህ ጥያቄ የጥቂት ስልጣን ጥመኞች ጥያቄ ሳይሆን የአንድ ሰላምና ዲሞክራሲ የጠማው ህዝብ ጥያቄ እንደሆነ ያሳይ። ሰባት ድርጅቶች ከፓሪስ ሆነው ያደረጉትን ጥሪ አሻፈረኝ ብለው አዲስ አበባ አትሰበሰቡም ሲሉ የሚኖረን የትግል አማራጭ አንድ ነገር ነው። በዚያው በሃገር ውስጥ ህዝቡ በገፍና በግልጽ ተንቀሳቅሶ ፍላጎቱን ካሳየ በኋላ አሻፈረኝ ቢሉ ደግሞ የሚኖረው የትግል አማራጭ ሌላ ነው። ሁሉም በጊዜው ይደርሳል።

<u>ጥያቄ</u>:- አስተባባሪ ኮሚቴው ባቀደውና ባደረገው ጥሪ መሠረት ስብሰባው በአዲስ አበባ ለማካሄድ ሲወሰን ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ምን ያህል አጋዥነት እንዳላቸው አጢኖ ተመልክቷቸዋል? ለስብሰባው አዲስ አበባ የተመረጠበት ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

<u>መልስ</u>:- ይህ "ለምን ለስብሰባው አዲስ አበባ ተመረጠ?" የሚለው ጥያቄ መጀመሪያ ሲመጣ በበኩሌ በጣም እንግዳ ነገር ሆኖ ነበር የታየኝ። **ኢትዮጵያውያን ስለኢትዮጵያ ችግሮች ለመወያየት ሌላ የት ይሰብሰቡ? ከዚህ ይልቅ መጀመሪያስ ቢሆን ፓሪስ ለምን ተሰበሰባችሁ ብላችሁ አትጠይቁም ወይ? ምንም ቢሆን እኮ አዲስ አበባ ሞቃድሾ፣ ኢትዮጵያም ሶማሊያ አይደለችም እያልኩ ነበር የምመልሰው። ግን በተደጋጋሚ ሲመጣ ነገሩም የተወሳሰበ መልሱም እንዲህ ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም።** ነገሩን በአጭር ለማስቀመጥ ብዙ ኢትዮ ጵያውያን ይህንን ጥያቄ ደጋግመው የሚያነሱ በሁለት ምክንያቶች ይመስሉኛል። በአንድ በኩል የዚህን አገር አቀፍ የሰላምና እርቅ ጉባኤ ጠንቀቆ ባለመረዳት ሁለተኛ ደግሞ በሃገሪቱ ያለውን የሃይሎች አሰላለፍና የኢህአዴግን ዲሞክራሲ ልኩን ጠንቅቆ ከመረዳት የሚፈልቁ ጥያቄዎች ይመስሉኛል። የስብሰባውን ምንነት ጠንቅቆ ያለማወቅ ነገር አለ። ይህ መቸስ የኛም ጉድለት ነው። አዲስ አበባ ስብሰባው ይደረግ ሲባል ብዙ ሰዎች የገባቸው ፓሪስ የተገናኙት ድርጅቶች ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችን ጨምረው እንደገና አዲስ አበባ ለመገናኘት ቀነ ቀጠሮ ብቻ ያረጉ የመሰላቸው አሉ። ከላይ እንዳልኩት ስብሰባው የተቃዋሚ ኃይሎች ስብሰባ ብቻ ሳይሆን ሁሉን አቀፍ ነው። ነጻ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ኢህአዴግ ራሱ፤ ኢህአዴግን የሚደግፉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ እንዲገኙ እንፈልጋለን። ከዚህም ውጭ ደግሞ ከፖለቲካ ውጭ የተደራጁ የሲቪል ሶሳይቲው ተወካዮች እንዲሳተፉ እንፈልጋለን። እንደዚህ በተሳታፊው ብዛትም ሆነ በተሳ ታፊው ዓይነት ሰፊ የሆነ ስብሰባ ሶስት መቶም፣ አራት መቶም ከዚያም በላይ ሰው ሊገኝበት ይችላል። ይህ ሁሉ ሰው ስለሃገሩ ጉዳይ ለመወያየት አገር ለቆ መሄዱ እስከዚህም አልታ የንም። ሁለተኛው ምክንያት ከዚህ ኛው ይበልጥ መሠረታዊ ይመስ ለኛል። የሃገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታና ሕዝቡ ስለ ኢህአዴግ ማንነት ከልምዱ ያገኘውን ግንዛቤ የሚመለከት ምክ ንያት ነው። ከፓሪሱ ጉባኤ ወዲህ በሃገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ከፍተኛ ለውጥ አለ። የሰላም መፈክር ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ፈር እየቀ የረች ትታያለች። በአንድ በኩል ከኢህአዴግ ነጻ የሆኑ ኃይሎችና ተቃዋሚ የሆኑ ኃይሎች /ለኢህአዴግ አመራር ሁለቱም አንድ ቢመስሉም/ በግልጽ፣ በይፋ፣ በተግባር የሰላ ምና የእርቅ ኃይል መሆናቸውን እያሳዩ ናቸው። በሌላ በኩል ኢህአዴግ አለ።

"የሰላም ጉዳይ እናንተን አያገባችሁም" ማለቱ ይሁን ወይስ "የሰላም ጉዳይ እኔን አያገባኝም" ይበል ገና በውል ባይታወቅም "እኔም አልገኝም" እናንተም አትሰበሰቡም" እያለ ነው። እንደዚህም በመሆኑና በተለይም አገር ቤት ይህንን ጥሪ በደገፉ ድርጅቶች ላይ በመካሄድ ላይ ያለው ማሳደድ ተጨምሮበት በብዙ ኢትዮጵያውያን ዓይን የሰላም መፈክር የተቃዋሚና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች መፈክር ሆና እየታየች ነው። ራሱ ኢህአዴግ ባመጣው መዘዝ የተነሳ የሰላምና የዲሞክራሲን ጥያቄ የተቃዋሚዎች ሞኖፖል አርጎ የማየት አዝማሚያ አለ። ለዚህ ነው ሌላው ቀርቶ እናንተ እንኳን አንዳንዴ ይህንን ጉባኤ "የተቃዋሚ ኃይሎች ስብሰባ" ለማለት የሚቃጣችሁ። ብዙ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ተጨባጭ የሆነ ግንዛቤ ስለሚነሱ ይህንን ጉባኤ አዲስ አበባ እናደርጋለን ስንል "ሰዎቹ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አልገባቸውም ወይም አጉል ለከፋ /ፕሮቮካሲዮ/ ይዘዋል" እስከማለት የሚቃጣቸው። ለዚህ ነው "እንዲህ የሚሉት ምን ዋስትና አግኝተው ነው?"እያሉ የሚጠይቁት። በሃገራችን ያለው ትንሽ ለየት ያለ ዲሞክራሲና ኢህአዴግ ተቃዋሚ ብሎ ለሚሰይማቸው ኃይሎች ምንም ቦታ የሌለው ዲሞክራሲ መሆኑን ተገንዝበዋልና። እንዲህ ዓይነቱ ስብሰባ በውስጥና በውጭ ያለውን ሁኔታ በሚመለከት አመቺ ነው ወይ ለተባለው ጥያቄ መጀመሪያ እስቲ አንድ ነገር ላንሳ። ሃላፊነት የሚሰማቸው የፖለቲካ ታጋዮች ከአንድ ከሆነ ችግር ህብረተቡ እንዲወጣ ርምጃ ሲጠቀሙ ሁኔታው ይህንን ርምጃ ለመውሰድ አመቺ ነው ወይ የሚለውን ጥያቄ የሚያመጡት በሁለተኛ ደረጃ መሆን አለበት። እኛ ኢትዮጵያ ካሉችበት ችግር ተሰብስቦ ከመወያየት ሌላ መፍትሄ አልታየንም። ይህ ነው መንገዱ ኑና እንወያይ ብለን እንደኛው ስለሰላምና ስለህዝባችን የሚጨነቁ ኃይሎችን ጋብዘናል። ዋናው ይህ ነው። ከዚህ በኋላ ነው አመቺ ሁኔታ ካለ ለማጎልበት ከሌለ ደግሞ ለመፍጠር መታገል የሚያስፈልገው። እንዲህ ዓይነት አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ደግሞ ሁሉም አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት። የሆነ ሆኖ ግን በውስጥም በውጭም አጋዥ የሆነ ሁኔታ አለ ብለን እንገምታለን። በውስጥም የሄድን እንደሆነ በሃገራችን ባለው ሁኔታ ስጋት ያልወደቀ የህብረተሰብ ክፍል የለም። የፓሪሱ ጥሪ ከመደረጉ በፊት ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች አንድ ሁሉን አቀፍ የሆነ ሃገራዊ ኮንፈራንስ እንዲጠራ በተደጋጋሚ ጥሪ አርገዋል። ይህ የጋራ ጥሪም ሲደረግ ድጋፍ የመጣልን ከየአቅጣጫው ነው ማለት ይቻላል። ሌላው ቀርቶ ከዚያ ወዲያ ኢህአዴግ ይህንን ሀሳብ ለማስወገዝ በያለበት የሚያስደርጋቸው የትእዛዝ ሰልፎች የጉባኤውን መንፈስና ዓላማ ለማክሸፍ የሚያደርገው መሯሯጥ ይህ የህዝብ ድጋፍ እንዳስደነገጠው የሚያሳይ ነው። ችግሩ የደጋፍ ማነስ ነው። በሃገር ውስጥ በይፋ እንዳይገለጽ ኢህአዴግ በልዩ ልዩ ጸረ ዲሞክራቲክ ዘዴዎች፣ በተለያዩ ሸሮችና ማስፈራሪያዎች መጠቀሙ ነው። በውጭ ዓለምም የሄድን እንደሆነ በዛሬይቱ ዓለም ከሚያዩት አሰቃቂና አስከፊ የርስ በርስ ጦርነቶች ትምህርት በመቅሰም ያለው ሁኔታ ከቁጥጥር ውጭ ከመውጣቱ በፊት መፍትሄ ይፈለግ የሚሉ ብዙ ናቸው። የአውሮፓ ፓርላማ የእንደዚህ ዓይነቱን ጉበኤ ሃሳብ አምኖበት አገር አቀፍ ጉባኤ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀባይነት ሌላ መንግሥት እንዲቋቋም የጠየቀው። በአሜሪካም የሄድን እንደሆነ የኮንግረሱ የሰው ልጅ መብት ኮንሚሽን መሪዎች በይፋ፣ በደብዳቤ ሃገሪቱ ወደባሰ ጦርነት እንዳትገባ ውይይት ይከፈት ብለው የጠየቁት ከፓሪሱ ስብሰባ በፊት ነው። በፓሪሱ ስብሰባ ጊዜም የአውሮፓ ፓርላማ መሪዎች ከራሱ ከፕሬዜንዳቱ አንስተው ጉባኤውን ደግፈው መልእክት አስተላልፈዋል። ከዚያም ወዲህ በእውነቱ ያለው ድጋፍ ከፍተኛ መሆኑን ያደረግናቸው ግንኙነቶች አረጋግጠውልናል። እንዲያውም የዚህ ጥሪ አስፈላጊነትና ወቅታዊነት እጅግ ግልጽ ከመሆኑም የተነሳ ኢህአዴግ እዚህ ጉባኤ ላይ አልገኝም ብኋል ስንላቸው በጣም ይገረማሉ። ከዚያ አልፈን ደግሞ እናንተም አዲስ አበባ አትሰበሰቡም እያለ ነው ብለን ስንነግራቸው ጨርሶ አያምኑንም። በጎን የነሱ ተወካዮች እየሄዱ በሃገሪቱ ዲሞክራሲ አለ የሰው ልጅ መብት ይከበራል ስለሚሏቸው የዚህ ስብሰባ መከልመል ጨርሶ አይገባቸውም። በቅርቡ በአሜሪካ ኮንግረስ በኢትዮጵያ ሁኔታ በተደረገው ውይይት ፕሮፌሰር ማሪና ኦታዌ የተባሉት ምሁር በሰጡት ቃል እንደ ምናየው ከሆነ ግን እሳቸው የኢህአዴግን ዲሞክትነት ልክ በተሻለ የተገነዘቡ ይመስላሉ። እንዲህ ዓይነቱ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ለሃገሪቱ የተወሳሰበ ችግሮች ሁሉንም የሚያሳትፍ መፍትሄ ከመሻት በፊት ምርጫ የሚለውን ነገር ካካሄደየአሜሪካንመንግሥት ታዛቢዎች በመላክ እንዳይተባበር ጠይቀዋል።

<u>ጥያቄ:</u>- በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለወት?

<u>መልስ</u>: ይህንን የፓሪስ ጥሪ አጋጣሚ ፈቅዶላቸው ሰባት ድርጅቶች አደረጉት እንጂ የሰላምና የዲሞክራሲ ናፍቆት የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነ እናውቃለን። ለዚች አገር በጎውን የሚመኙ በዓለም አቀፍ ደረጃም ያሉ ኃይሎች እንዲደረግ ያላቸውን ከፍተኛ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ውጤቱም በከፍተኛ ጉጉት እንደሚጠባበቁ መገንዘብ ችለናል። ከእንግዲህ የዚህ ጉባኤ በኛ እጅ ሳይሆን በውጭም በውስጥም ባሉ ኢትዮጵያውያን እጅ ነው። ሁላችንም ወደምንመኘው ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ አንድነትና በልጽግና ለመጓዝ የሚያስችለንን የብሔራዊ ውይይት ጎዳና ጠቁመናል። ለዚህ ዓላማ ህዝቡ በግልጽና በገፍ ከተባበረን፣ ይህንን ድጋፍ ደግሞ የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲ /የኢህአዴግ ጭፍን ወዳጆች ሳይቀሩ/ እንዲያየው ከተደረገ ይህንን ጉባኤ ማንም ሊያስቀረው አይችልም። ስለዚህ የኮሚቴው ጥሪ ሁሉም ይንቀሳቀስ። ሁሉም ይተባበረን የሚል ጥሪ ነው።